
# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2017 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋፅዖ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገፅታዎች ተጠናክረው በመቀጠላቸው በተለይ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ስፍራዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የነበረ ሲሆን፤ በተለይም ለረጅም ጊዜ ዝናብ ያልነበራቸው የደቡብ የሀገሪቱ ስራዎች በአሥሩ የመጨረሻ ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከባድ ዝናብ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በአዲስ አበባ ኦብዘርባቶሪ 42.0፣ በአይራ 79.5፣ በአርጆ 44.0፣ በቡለን 66.7፣ በቦሬ 47.7፣ በድሬዳዋ 43.1፣ በዳንግላ 50.9፣ በዲላ 52.7፣ በጋምቤላ 44.0፣ በጎንደር 61.4፣ በሊሙገነት 45.0፣ በመኢሶ 42.0፣ በማይጸምሪ 48.0፣ በኑራኢራ 52.0፣ በሽራሮ 55.5፣ በሲርባ አባያ 40.4፣ በላሬ 53.1፣ በከማሺ 67.1 እና 45.0፣ በሶጊ 41.8 እና 80.1 እንዲሁም በካራቆሬ 82.3 በሚሊ ሜትር ይገኙበታል።


ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-243 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከትግራይ የምዕራብ ትግራይ፤ የአማራ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የጋምቤላ፤ ከኦሮሚያ ከቦረና ዞኖች በስተቀር፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ ከትግራይ የደቡብና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች፤ የአፋር ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የፊቅና የደገሀቡር ዞኖች ከ5-25 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ4 ላልበለጡ ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2)።

በአጠቃላይ ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር ከትግራይ የምዕራብ፣ የመካከለኛውና የምስራቅ ትግራይ፤ የአማራ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የጋምቤላ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ አብዛኛው ኦሮሚያ፤ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ እንዲሁም ከአፋር፤ ዞን 3 እና 5 መደበኛ እና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው በታች የሆነ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)።


ካርታ1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ3 ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

ባለፉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋፅዖ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገፅታዎች ተጠናክረው በመቀጠላቸው የምዕራብ፣ የመካከለኛወና የምስራቅ ትግራይ፤ የአማራ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የጋምቤላ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ አብዛኛው ኦሮሚያ፤ ድሬዳዋና ሐረሪ፤ እንዲሁም ከአፋር፤ ዞን 3እና 5 መደበኛ እና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ላይ ተስተውሎ የነበረው የዝናብ ሁኔታ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች እንደ ማሽላና በቆሎ የመሳሰሉት እንዲሁም በክረምት ወቅት ተዘርተው በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬ እህሎችና የቅባት እህሎች ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታው የጎላ ነበር። በሌላ መልኩ ለረጅም ጊዜ ዝናብ ያልነበራቸው የደቡብ የሀገሪቱ ቦታዎች በአሥሩ የመጨረሻ ቀናት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ በማግኘታቸው በአካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ እንደነበረው እሙን ነው። ይሁን እንጂ ከክረምቱ ዝናብ መጠናከር ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ከባድ ዝናብ፤ ዝናብ አጠር ለሆኑና ዉሃን የማቆር ሥራዎችን ለመከወን፣ ለግጦሽ ሣር መሻሻልና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን የደረሰን ሪፖሪት ባይኖርም በረዶ ቀላቅሎ የጣለዉ ከባድ ዝናብ በአንዳንድ ሥፍራዎች በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች እና ቋሚ ተክሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደነበረዉ ይገመታል፡፡ እንዲሁም በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት የሚታወቁና የመሬት አቀማመጣቸው ተዳፋትና ውሀ ገብ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የነበረው የእርጥበት መብዛት አሉታዊ ጎን እንደነበረው እሙን ነው፡፡


## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1-10/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 1-10 ከሴፕተምበር 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የላይኛውን ክፍል ያዳረሰ መሆኑ ተስተውሏል። በመሆኑም አብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣

የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ጥቂት የላይኛው አዋሽ እንዲሁም ጥቂት ኪስ ቦታዎች በሆኑ የላይኛው ዋቢሸበሌና የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው። በሌላ በኩል የመካከለኛውና የታችኛው አዋሽ፣ የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ገናሌዳዋና ዋቢሸበሌ እንዲሁም ጥቂት ኪስ ቦታዎች በሆኑ የአባይና የተከዜ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ በተቀሩት የተፋሰሶች ክፍል ላይ ግን ከፊል ደረቅና ደረቃማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው። በሌላ በኩል በተለይ ከባድ ዝናብ የተመዘገበባቸው ተፋሰሶች ለውሃ ሀብት ግብዓት መጨመር ከፍተኛ አሰተዋፆ አድርጓል። በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በነበረው ከባድ ዝናብ ምክኒያት ቅፅበታዊ ጎርፍና የወንዝ ሙላት አስከትሏል (ካርታ 4)።

ካርታ 4 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 1-10/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# <u>እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11-20/2017 የሚኖረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በመደበኛ ሁኔታ በሴፐቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እየተዳከሙ የሚሄዱበትና ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በጎላ መልኩ እየቀነሰ በሂደትም የሚያቆምበት ጊዜ ነው፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ደግሞ  አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቆይታ ሊኖራቸው የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታን ሊፈጥሩ ይችላሉ። በዚህም መሰረት የዘንድሮው የክረምት ዝናብ ከሞላ ጎደል መደበኛውን ፈር ተከትሎ እንደሚወጣ የሚጠበቅ ቢሆንም፤ በአንዳንደ የሰሜን ምሥራቅ፣ በሥምጥ ሸለቆና በምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአወጣጥ ረገድ በመጠኑም ቢሆን የመዋዠቅ አዝማሚያ ሊኖረው ይችላል።

በአጠቃላይ ለሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከከተነበዩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጥንካሬን አንጻራዊ ግምት ውስጥ በማስገባት፤ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የሚጠበቅ ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም ይችላል። በተጨማሪም በዚህ ጊዜ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሚሆነው እና ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩት የደቡባዊው የኢትዮ□ያ ክፍሎች ላይ ከቀን ወደ ቀን የደመናው ሽፋን እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት <u>የምዕራብና የመካከለኛው ትግራይ ዞኖች፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ የጋምቤላ ክልል፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አገው አዊ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምሥራቅ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ የአርሲና የቦሌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ እንዲሁም የሲዳማ እና የጌዲዮ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና በጥቂት ቦታዎች ላይ</u>

ደግሞ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊከሰት ይችላል። በተጨማሪም ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ዋግ ህምራ፤ የትግራይ ምሥራቃዊና ደቡባዊ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፤ ድሬዳዋ እና ሀረሪ፣ የጌዲዮና የቦረና ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል ጅግጅጋ፣ ሲቲ፣ ደጋሀቡር፣ ጎዴ እና ፊቅ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ህዝቦች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

## እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እቀነሰ እንደሚሄድና በሂደትም የሚያቆምበት ነው፡፡ ቀደም ብለው የተዘሩ ሰብሎች በአብዛኛው ፍሬ በመሙላት ወደ መብሰል የሚደርሱበትና በአንዳንድ አካባቢዎችም የሰብል ስብሰባ ሊካሄድ የሚችልበትም ጊዜ ነው፡፡ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ እርጥበቱ አስቀድሞ በሚወጣባቸው አካባቢዎች የአረንጓዴ እፅዋት ሽፋኑ ቀስ በቀስ እየቀነሰ የሚሄድበትም ጊዜ ነው፡፡ በሌላ አንፃር ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች የግብርና ስራ እንቅስቃሴ የሚጀምሩበት ወቅት ሲሆን፤ በሂደትም የአረንጓዴ እፅዋት ስርጭትና የግጦሽ ሳር ልምላሜ እየጨመረ የሚሄድበትም ጊዜ ነው፡፡ በትንበያው ላይ እንደተገለፀው በሚቀጥለው የሴፕቴምበር ሁለተኛው አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው አሁን እየታየ ባለው መልክ ሊቆይ እንደሚችልና መደበኛውን ፈር ተከትሎ እንደሚወጣ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በአብዛኛው ለግብርናው ዘርፍ ገንቢ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ቀደም ብለው ለተዘሩና ፍሬ በመያዝ ላይ ለሚገኙ፤ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የውኃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብብና ወደ ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙና አልፎ አልፎም ከባድ ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል በትንበያው በተጠቀሱት አካባቢዎች አስቀድሞ

ልዩ ትኩረትና ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚመከር ሲሆን፤ በተለይም ሰብሎች በጎርፍ እንዳይበላሹ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድርግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ አንፃር በአንዳንድ አካባቢዎች ሰብሎች እየደረሱ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባ እየተከናወነ ሲሆን፤ የሚጠበቀው እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያሰፈልጋል፡፡

## እ. ኤ. አ ከሴፕቴምበር 11-20/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በበዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ትንበያው የሚያመለክት በመሆኑ፤ ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይም የተሻለ የእርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል።

በዚሁ መሰረት አብዛኛው የተከዜ፣ የአባይ፣ የባሮአኮቦ፣ የኦሞጊቤ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽና ስምጥሸለቆ፣ የላይኛው ገናሌዳዋና ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የታችኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆና ባሮአኮቦ እንዲሁም የመካከለኛው ዋቢሸበሌ መጠነኛ የሆነ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በሌላ በኩል በተቀሩት የተፋሰሶች ቦታዎች ላይ ከፊል ደረቅና ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል። በሌላ በኩል በተለይ የዝናብ ስርጭታቸው ከመደበኛ በላይ የሚጠበቅባቸው አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ስለሚኖርና የወንዞች ሙላት ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡